**ሳምንታዊ ዜና (ነሐሴ 10 ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ምሁራን የእርስ በእርስ ሽኩቻቸው እያየለ መጥቷል፣ ተማሪዎችም የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንዳይኖራቸው ምሁራኖች እየሰሩ መሆኑ ተጋለጠ፣ የኑሮ ውድነቱ በከፍተኛ ሁኔታ እየተስፋፋ መሆኑ ታወቀ፣ 1 ኩንታል ጤፍ 1350 ብር ደረሰ፣ በምርጫ 97 ተቃሚዎችን ደግፋችኋል የተባሉ የጐንደርና የጐጃም ነዋሪዎች እርዳታ ተከለከሉ፣ የአማራ ክልል ፕሬዝዳንት አያሌው ጐበዜና የአፋር ክልሉ ፕሬዝዳንት እስማኤል አሊሴሮ የሕዝብ ገንዘብ መመዝበራቸው ተጋለጠ፣ የወያኔ ባለሥልጣናት ጤፍ ለውጪ ኩባንያ እየቸበቸቡ መሆኑ ታወቀ፣ ወያኔና ሻዕቢያ በድንበሩ አካባቢ አሁንም ወታደራዊ ኃይላቸውን እያጠናከሩ ነው»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»**

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ ……………………**

በወያኔ ጫማ ስር ተንበርክኮ ሳይጠሩት አቤት ሳይልኩት ወዴት እያለ የኖረው እንድርያስ እሸቴ ላገለገለበት ወያኔያዊ ተልዕኮ ድርጐ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት እንዲሆን የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ከሾመው ወዲህ በግቢው ውስጥ ባሉ ምሁራን መካከል ከፍተኛ ክፍፍል ተፈጥሮ የተማሪዎቹንም ሞራል እያደቀቀት መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል::

ለሀገርና ለሕዝብ የሚያገለግሉ ብዙ ዜጋ ያፈራሉ ተብሎ የተነገራላቸው እነኚሁ የዩኒቨርስቲው ምሁራን ተብየዎች የወያኔው ተላላኪ ፕሬዝዳንት እንድርያስ በዘረጋላቸው የከፋፍለህ ግዛ ጐዳና ውስጥ ተጠልፈው በመግባታቸው የተነሳ በዘርና በጐሳ እንዲሁም በጐጥ ተከፋፍለው የግል ጥቅማቸውን ብቻ በማሳደድ ላይ መሆናቸውን ምንጮች ገልፀው በአሁን ሰዓት ዩኒቨርስቲው ውስጥ ያሉ ምሁራን መካከል የተከሰተው ቡድናዊ ስሜት ወደ ተማሪዎቹ ሳይቀር ወርዶ በሚያሳፍርና በሚያሳዝን ደረጃ ላይ መድረሱን ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል::

በሕዝብ ላይ በረሀ አመጣሽ ከሆኑት ከወያኔ በባለሥልጣናት አኩል ሲያሾፍና ሲቀልድ የቆየው ይኸው ተላላኪ ግለሰብ ለዩኒቨርስቲው ፕሬዝዳትነት ከተመደበ በኋላ ባደረገው የመከፋፈል ዘመቻ ተጠልፈው የክፍፍሉ ሰለባ የሆኑት ምሁራኖቹ ዛሬ በሀገርና በሕዝብ ላይ የሚደርሰውን በደልና ግፍ ከመቃወም ይልቅ የግል ጥቅማቸውን በማስቀደማቸው በዩንቨርስቲው ግቢ ውስጥ ህብረትና አንድነት መጥፋቱን የገለፁት ውስጥ አዋቂ ምንጮች እንድርያስ እሸቴ የተባለው የወያኔው ተላላኪ ለሕክምና አሜሪካ ሀገር ባለበት ቦታ ሆኖ እንኳዋን አሁንም እንደልቡ ምሁራኑን እያሽከረከራቸው መገኘቱ ምሁራኑ በራስ የመተማመን መንፈስ በውጣስቸው እንደሌለ አመላካች ነው ሲሉም አስረድተዋል::

ድንገት በተኛበት የቀረው የወያኔው ጉዳይ አስፈፃሚ የሆነው እንድርያስ እሸቴ ለብዙ ወራት በጦር ኃይሎች ሆስፒታል ሕክምና ቢደረግለትም በሀገር ውስጥ መዳን እንደማይችል ሐኪሞቹ በመናገራቸው ወደ ደቡብ አፍሪካ የተላከ ቢሆንም እዚያም ሕመሙ በመባባሱ ወደ አሜሪካ ለመንዝ የተገደደው ይኸው ግለሰብ በዊልቸር ላይ እየተሽከረከ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን አሁንም እያመሰ መገኘቱ የሚያሳፍርና የሚያሳዝን ነው ያሉት አንድ የዩኒቨርስቲው መምህር በአዲስ አበባ

ዩኒቨርስቲ ውስጥ ከማስተማር ይልቅ ለግል ተቋም ተቀጥሮ መስራት የተሻለበት ደረጃ ላይ ደርሰናል ሲሉ እያዘኑ ገልፀዋል::

ህዝብን ከችግርና ከመከራ የሚያወጡ ብቁ ዜጎች ያፈራሉ ተብሎ ተስፋ ተጥሎባቸው የነበሩት ምሁራኖች እንደ ጡጦ የሚጠባ ሕፃን በአንድ ግለሰብ እየተሽከረከሩ ስለ ግለ ጥቅማቸው እንጂ ስለሐገርና ወገን ማሰብ ማቆማቸው አሳፋሪ ከመሆኑም በላይ አሳዛኝ ነው ያሉት እኝሁ ምሁር በግቢው ውስጥ ያለው በዘር መከፋፈል አሁን አሁን ተባብሶና ተስፋፍቶ በጐጥና በመንደር ሆኗል ካሉ በኋላ ተማሪዎቻቸውንም የዚሁ ሰለባ ለማድረግ አንዳንድ መምህራኖች የሚያደርጉት ቅስቀሳ ከአንድ ምሁር ነኝ ከሚል ሰው የማይጠበቅ የወረደና የዘቀጠ ተግባር ነው ሲሉ በአልህና በቁጭት ገልፀዋል::

ከ13 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ በችግር እየተጠበሰ ባለበት፣ ሌላውም ሕዝብ በኑሮ ውድነት መላወስ ተቸግሮ ባለበት በዚህ ወቅት ለሀገርና ለወገን መፍትሄ ያቀርባሉ ተብሎ የሚጠበቁት እነኚሁ ምሁራን ተብየዎች እርስ በርስ ጊዜው ባለበፈት ወያኔ በቀደደው መንገድ ተጉዘው ይህን የመሰለ ተልካሻ ተግባር ውስጥ መገኘታቸው በእጅጉ የሚያሳፍር ከመሆኑም ባሻገር ህዝብና ሀገርን እየቀበሩ መሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል ሲሉም አክለው ገልፀዋል::

በቅርቡ ይኸው እንድርያስ እሸቴ የተባለው የወያኔው ጉዳይ አስፈፃሚ እንኩዋን አሜሪካ ሆኖ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት አድርጐ የሾማቸውን ዶ/ር ቡቴ ጉቱን በፋክስ መልዕክት ብቻ አባርሮ ፕሮፌሰር ፅጌ ገብረማርያምን ከተካ በኋላ በግቢው ውስጥ የቡድናዊ ስሜቱ ጐልቶ የወጣ ሲሆን በወቅቱ ይህ እርምጃ ሲወሰድ የተበሳጩ ምሁራኖች ስራችንን እንለቃለን እንዲህ ያለ ጐጠኝነት የተጠናወተበት ግቢ መስራት አንፈልግም ብለው መልቀቂያ ያቀረቡ ቢሆንም በእንድርያስ እሸቴ ትዕዛዝ እንደተከለከሉ የገለፁት ምንጮች አሁንም በውስጣቸው ያለውን ጐጠኝነት ስሜት ጨርሰው አውጥተው ካልጣሉ በስተቀር በግቢው ውስጥ እጅግ አደገኛ ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል ስጋታቸውን ይገልፃሉ::

አምና የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራኖችን ሰብስቦ ባነጋገረበት ወቅት በጥያቄ ያጣድፉታል ተብሎ ሲጠበቅ መኖሪያ ቤትና መኪና ይሰጠን ብለው መላው የሀገሪቷን ሕዝቦች ያሳፈሩና ተልካሻ ጥያቄ ማቅረባቸውን የተከታተሉ አንድ ከውጭ ሀገር የመጡ ኢትዮጵያዊ በዜግነቴ አፈርኩ፣ የዩኒቨርስቲ መምህር ማለት ቅድሚያ ለሕዝብና ለሀገር የሚል ነበር የማውቀው አሁን ግን ለኔ ብለው የሚጠይቁትን ነው ያየሁት ከነዚህ ምን ሊገኝ ይችላል? ሲሉ በትዝብት ገልፀዋል::

በወያኔ የሚሰነዘርባቸውን ጥቃት እንኩዋን ለመከላከል እንዳይችሉ ህብረታቸውንና አንድነታቸውን ንደው እንደ ቦይ ውሃ በተቀደደላቸው መንገድ የሚጓዙት እነኚሁ ምሁራን ነን ባዮች ከገቡበት ስህተት ወጥተው ተማሪዎቻቸውንና ወገናቸውን መርዳት ግድ ይላቸዋል ያሉት ሌላው የአዲስ አበባ

ዩኒቨርስቲ መምህር ለህዝብና ለሀገር አስበው የሚሰሩትን መምህራኖች እያደኑ በተማሪዎቻቸው መጥፎ ስያሜ እንዲሰጣቸው ማድረጋቸው የዚሁ የቡድናዊ ስሜት አንዱ አካል ነው ሲሉም ይገልፃሉ።

ፕሮፌሰር እንድሪያስ እሸቴን የሾመው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ሲሆን፣ የቅርብ ተጠሪነቱም ለመለስ በመሆኑ ለትምህርት ሚኒስቴር አልታዘዝም እያለ በማስቸገሩ በሁለቱ የወያኔ ባለሥልጣናት መካከል ከፍተኛ ሽኩቻ እንዳለም የትምህርት ሚኒስትር ምንጮች ገልፀዋል።

የስራ እንቅስቃሴውን ለትምህርት ሚኒስቴር ሪፖርት ማቅረብ አለብህ ተብሎ ቢነገረውም ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን ውጭ ታሳድራለች እንዲሉ እንድሪያስ የመለስን ተልዕኮ በአጥጋቢ ሁኔታ እየተወጣ ስለነበር የትምህርት ሚኒስትሩን ስንታየሁን ትዕዛዝ አልቀበልም በማለቱ በሁለቱ ግለሰቦች መካከል ከፍተኛ ችግር ተከስቶ ያለ መሆኑን ምንጮች አክለው ገልፀዋል።

በአሁን ሰዓት በዊልቸር ሆኖ በአሜሪካ ውስጥ ሕክምናውን እየተከታተለ ያለው የወያኔ ጉዳይ አስፈፃሚ እንድርያስ በ1983 ዓ.ም ሻዕቢያ አስመራን ሲቆጣጠር በርካታ ኢትዮጵያውያን በፒንሳ የወርቅ ጥርሳቸው ሲነቀል እያየ ጥሩ እንክብካቤ ተደርጎላቸዋል በማለት እጅግ አሳፋሪና በኢትዮጵያዊያን ሞትና ስቃይ ላይ የተሳለቀ ግለሰብ እንደነበር ያስታወሱት አንድ መምህር አሁንም ቢሆን በምሁራኑ መካከል ከፍተኛ ክፍፍል እንዲፈጠር ያደረገው ይኸው ግለሰብ ነው ሲሉም ገልፀዋል።

የወያኔ ቡድን በሀገርና በሕዝብ ላይ በሚሰራው ግፍ ምክንያት የራሱ አገልጋይ ካድሬዎች ሳይቀር እየከዱ ወደውጭ ሀገር እየተሰደዱ መሆኑን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል።

ባለፈው ሳምንት የተወካዮች ምክር ቤት አባል የመንግስት ወጪ አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባል የነበረው በለጠ ኢታና የተባለው ግለሰብ ስርዓቱን ከድቶ እንግሊዝ የጥገኝነት ጥያቄ ማቅረቡን ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል።

የኦህዴድ አባል በለጠ ኢታና በተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ወጪ አስተዳደር ኮሚቴ ውስጥ አባል የነበረና ለ15 ቀን ያህል ትምህርት ለመቅሰም ወደ እንግሊዝ ሐገር የተላከ ቢሆንም «እናንተ ኦህዴዶች ንብ መስላችሁ ስትፋቁ ዝንብ ናችሁ» እየተባልን ከሕወሓቶች ጋር አንሰራም በማለት በዚያው ጥገኝነት የጠየቀ መሆኑን ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በደልና ግፍ ለ17 ዓመታት ሲፈፀምበት አይቶ እንዳላየ፣ ሰምቶ እንዳልሰማ ሆኖ ነበር የዘለቀው ዛሬ ሁኔታው እንደቀድሞ አልቀጥል ቢለው ለህዝቤ ስል ስርዓቱን ከድቻለሁ ሲል ማስመሰያ ቢናገርም እስከዛሬ ድረስ ከወያኔ ጋር አብሮ በሕዝብ ላይ ለፈፀመው በደልና ግፍ ታሪክና ትውልድ መቼም ቢሆን ቅጣቱን የሚሰጠው መሆኑን እነዚሁ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል።

በሀገሪቱ የተፈጠረው የኑሮ ውድነት ከዕለት ወደ ዕለት እየተባባሰ መምጣቱን ከተለያዩ አካባቢዎች የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

በአሁኑ ሰዓት በመላ ሀገሪቱ በተፈጠረው የኑሮ ውድነት የተነሳ ዜጎች የዕለት ጉርስ መቅመስ ተቸግረው እንዳሉ የደረሰን ዘገባ ገልፆ በሁሉም ሸቀጦች እና እህል ላይ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ እንዳሳየ ይኸው የደረሰን ዘገባ ገልጿል::

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሰሞኑን ግብይት እየተደረገ ያለው የጤፍ ዋጋ 1350 ብር ሲሆን፣ ዘይት በሊትር 29 ብር፣ ሞኮሮኒ 12.50፣ ስኩዋር 11 ብር፣ ቀድሞ 1.25 ሲሸጥ የነበረው ቀይ ሽንኩርት እንኩዋን 6.50 መግባቱን ይኸው የደረሰን ዘገባ አስታውቋል::

ይህ ሁሉ ችግርና መከራ በህዝቡ ላይ እየደረሰ መሆኑን ያወቀው ወያኔ ያለ አንዳች ርህራሄ በሕዝቡ ስቃይና እንባ እየተደሰተ ከመሆኑም ባሻገር የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ከውጭ ስንዴ አቀርባለሁ እያለ እየተሳለቀና እያሾፈ መሆኑ ከተግባሩ ለማረጋገጥ ተችሏል::

ሀገር በታኝና ከፋፋዩ የወያኔ ቡድን ያለበትን ግዴታ ከመወጣት ይልቅ በሕዝብ ስቃይ እየተደሰተ በመከራውም እያሾፈ ከመሆኑም በላይ በችግር ላይ ችግር እየደራረበበት መውጫ ከሌለው የችግር አረንቋ ውስጥ እየከተተው መሆኑ ታውቋል::

የወያኔው መሪ ከ3 ወር በፊት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለተባለው ባቀረበው ሪፖርት ገበያውን ለማረጋጋት ከውጭ ስንዴ በርካሽ ዋጋ እናስገባለን በማለት ገልፆ እንደነበረ ያስታወሱት አንድ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ስንዴ በ3 ወሩ መጥቷል ቢባልም ባላየነውና ባላረጋገጥነው ነገር ቅድሚያ ክፍያ ክፍሉ ተብለን እየተገደድን ነው ሲሉ ገልፀዋል::

በዚህ ቀውጢ ወቅት ከተቻለ ከመንግስት ካዝና ወጪ ተደርጐ በነፃ ማደል በተገባ ነበር ይህ ካልሆነለት ደግሞ እህሉን አሳይቶ መሸጥ ሲገባ በቅድሚያ ገንዘብ ክፈሉ እያለ መወትወቱ በካዝና ውስጥ ምንም ተቀማጭ ገንዘብ እንደሌላቸው ያረጋገጠ ጉዳይ ነው ብለዋል::

ከሕዝብ ሕይወት ይልቅ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም የሚዳክረው የወያኔው ቡድን በሁሉም አቅጣጫ ገንዘብ ማግበስበስና የጦር መሣሪያ መሸመት ቀን ተቀን ስራው አድርጐ እየተንቀሳቀሰ ከመሆኑም በላይ በሕዝብ ስም የገባውን እርዳታ ጭምር ለመሣሪያ መግዣ እያዋለው በመሆኑ ሕዝቡን ለከፍተኛ ችግር ዳርጐታል ያሉት አንድ የኢኮኖሚ ባለሙያ በአሁን ሰዓት የተከሰተው የኑሮ ውድነት እጅግ ስር የሰደደ በመሆኑ በቀላሉ ሊቀረፍ ይችላል የሚል ግምት የለኝም ሲሉ ስጋታቸውን ገልፀዋል::

የወያኔ ባለሥልጣናት በሕዝብ ገንዘብ እንደልባቸው እየተምነሸነሹ ሕዝቡን ለኑሮ ውድነትና ለድህነት ዳርገውት መልሰው ችግርና የኑሮ ውድነት የለም እያሉ እየተሳለቁበት ከመሆኑም  በላይ ሰሞኑን በወያኔው መሪ መለስና በባለሥልጣናቱ መካከል ሁለት የተምታታ መግለጫ ተሰጥቷል።

ሰሞኑን በሀገር ውስጥ የግብርናና ገጠር ልማት ሚነስቴር ምክትል ሚኒስቴር አቶ አበራ ደሬሳና የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሲምኦን መቻሌ አማካኝነት ዲፕሎማቶችና የውጭ ጋዜጠኞችን ሰብስበው «ረሀቡ በሀገሪቱ ስር የሰደደ ደረጃ ላይ መድረሱንና በቀጣዮች ቀናትም ሊባባስ እንደሚችል» ገልፀው የእርዳታ እጃችሁን ዘርጉልን በማለት ሲማፀኑ በተጓዳኝ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ደግሞ ታይምስ ለተባለው ታዋቂ መፅሄት በሰጠው ቃለ ምልልስ «በሀገሪቱ የከፋ ረሀብ አልተሰከተም፣ የተራቡት ቦታዎች ኪስ ናቸው» በማለት በህዝብ ሞትና ስቃይ ተሳልቋል።

ወትሮም ለሕዝብና ለሀገር ክብር የሌለው የወያኔው መሪ ከ13 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ በረሀብ እየተቆላ ገሚሱም ወደሞት እያመራ ባለበት በዚህ ወቅት የተከሰተው ረሀብ መጠነኛ ነው እያለ በህዝብ ከማሾፉም በተጨማሪ እርዳታ እንኩዋን እንደይሰጣቸው መንገዱን በለመደው ሀሰተኛ ቅስቀሳ እየዘጋጋው ይገኛል ሲሉም የእርዳታ ሰጪ ድርጅት ሰራተኞች በሀዘን ይገልፃሉ።

በተጓዳኝ በሀገር ውስጥ የወያኔ ባለሥልጣናት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ በረሀብ እንደተጉዳና አሁንም ቁጥሩ ሊያሻቅብ እንደሚችል ገልፀው የድረሱልን ጥሪ እያቀረቡ ሲሆን፣ የወያኔ መሪዎች እርስ በእርስ የተምታታ መግለጫ መስጠታቸው በእጅጉ ትዝብት ላይ የጣላቸው መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል።

የኑሮ ውድነቱ፣ ረሀብ፣ ችግር ተደማምሮ ከመኖርና አለመኖር መካከል እየዋለለ የሚገኘውን ህዝብ ከመታደግ ይልቅ ለስልጣን ማራዘሚያ የሚሆነውን ወታደራዊ ተቋም በከፍተኛ ወጪ እየገነባ መሆኑ ያሳዝናል ያሉት አንድ የአዲስ አበባ ነዋሪ ለሕዝቡ በገዛ ገንዘቡ የሚገዛውን እህል እንኩዋን በአግባቡ ለማቅረብ አለመቻሉ አሳፋሪና አሳዛኝ ነው ሲሉ በምሬት ገልፀዋል።

በቅርቡ በረሀብ ከተጠቁት የሀገሪቱ ክፍሎች መካከል ጐንደርና ጐጃም አንዱ ሲሆን ለዚህ አካባቢ ነዋሪዎች እርዳታ እንዲሰጥ ለጋሽ ድርጅቶች ቢያቀርቡም በ1997 ዓ.ም ተቃዋሚዎችን መርጣችኋል ተብለው ታስረው ለነበሩት ሰዎች በአሁን ሰዓት እንዳይሰጣቸው የወያኔ ግልገል ካድሬዎች እየከለከሉቸው መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልጿል።

በተለይም በጐንደርና በጐጃም የተራቡ ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙትን ሕዝቦች የተቃዋሚ ደጋፊ ናችሁ በሚል ለጋሽ ድርጅቶች የሰጡዋቸውን እህል እየነጠቁ «የመረጣችሁት ፓርቲ ይመግባችሁ» እያሉ በተራቡ ወገኖች ላይ ይህን መሰል ዘግናኝ እርምጃ መውሰዳቸው በእጅጉ አሳዛኝ ነው ያለው የደረሰን ዘገባ ወያኔ አሁንም ድረስ በሕዝቡ ላይ እየወሰደ ያለው አረመኔያዊ ተግባር እንደቀጠለ መሆኑን የሚያመላክት ነው ሲል የደረሰን ዘገባ አስረድቷል።

ለሱዳን መሬት መሸጡን ተቃውመው ቁጣቸውን የገለፁት የታች አርማጭሆ፣ በለሳ፣ ወልቃይት ጠገዴና ሌሎችም ወረዳዎች የሚኖሩትን ሕዝቦች ደግሞ ስትጮህለት የነበረው አካል ይቀልብህ እያሉ የወያኔ ግልገል ካድሬዎች በሕዝቡ ላይ እየተሳለቁ ከመሆኑም በላይ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አንዳችም እርዳታ እንዳይሰጣቸው ተከልክለው እንደሚገኙም ይኸው የደረሰን ዘገባ አስረድቷል፡፡

በተለይም የጉንደር ዞን ባለሥልጣናት በሕዝቡ ገንዘብ ማርቼዲስና ዘመናዊ የቤት አውቶሞቢል ገዝተው ቤታቸውን አዲስ አበባ ላይ አስገንብተው እንደልባቸው እየተምነሸነሹ ሕዝቡን መልሰው በረሀብ እንዲያልቅ ማድረጋቸው ወያኔያዊ አረመኔ ባህሪያቸው ተፀናውቷቸው የሚተገብሩት ነው ያለው የደረሰን ዘገባ በአሁን ሰዓት የዞኑ ባለስልጣናት በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ መዝብረው ለግል ጥቅማቸው እንዳዋሉት አብራርቷል፡፡

ከአማራ ክልል ፕሬዝዳንት ተብየው አያሌው ጉበዜ ጋር ተመሳጥረው በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የመዘበሩት የወያኔ የተላላኪ ካድሬዎች ምስጢሩ እንዳይጋለጥባቸው ቢሸፋፍኑትም ለህዝብ እይታ ሊሰወር ባለመቻሉ ሀቁ የተጋለጠ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገልፆ በተለይም አያሌው ጉበዜ የተባለው የክልሉ ፕሬዝዳንት ከነአዲሱ ለገሰ ጋር በመመሳጠር የአማራውን ሕዝብ ጉሮሮ እየዘጉ የራሳቸውን ኪስ እያደለቡ ነው ሲል አስረድቷል፡፡

በዚህም መሠረት አዲሱ ለገሰ በባህርዳር እጅግ ዘመናዊ ደረጃውን የጠበቀ ሆቴል አስገንብቶ ስራ የጀመረ ሲሆን፣ እነበረከት ስምኦንም ከ50 በላይ ባለ ተሳቢ ዘመናዊ የጭነት መኪኖችን ገዝተው ከጅቡቲ ያለ ተቀናቃኝ ለብቻቸው እየሰሩ መሆኑን ያጋለጠው የደረሰን ዘገባ ሕዝቡ በረሀብ እየተቆላ እነሱ በሕዝብ ገንዘብ መንደላቀቃቸው በታሪክና በትውልድ ተጠያቂ እና ንብረታቸውም አንድ ቀን ለሕዝብ መመለሱ አይቀሬ ነው ሲል አብራርቷል፡፡

በተመሳሳይ የሕወሓት አባሉና መስራቹ የአፋር ክልል ፕሬዝዳንት እስማኤል አሊሴሮ በአንድ አመት ብቻ ከ7 ሚለዮን ብር በላይ መመዝበሩን የዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት አጋልጧል፡፡

በእስማኤል አሊሴሮና በባለሥልጣናቱ በአንድ አመት ብቻ ከ7 ሚሊዮን ብር በላይ የተመዘበረ መሆኑን ያጋለጡት የዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት ሂሳብ ሰራተኞች በአሁን ሰዓት በደህንነትና በካድሬዎች ከፍተኛ እንግልት እየደረሰባቸው መሆኑን የገለፀው የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ ከመለስ ባለቤት አዜብ መስፍን ጀምሮ እስከ ግልገል ካድሬዎቹ ድረስ ሁሉም የሕዝብን ገንዘብ መመዝበራቸውን ኦዲተሮቹ ማረጋገጣቸውን ጠቆማው አጋልጧል፡፡

ከቪላ ቤት እስከ ትልቅ ኩባንያ ድረስ ባለቤት የሆኑት የወያኔ ባለሥልጣናት ሕዝቡ የዕለት ጉርስ መቅመስ አቅቶት እየተንገዳገደ ባለበት በዚህ ወቅት መልሰው አንዴ ረሐብ አለ ሌላ ጊዜ ደግሞ ረሐብ የለም በማለት እያሾፉበት መሆኑ ያሳዝናል ሲል የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ ያስረዳል፡፡

የሀገሪቱ ሕዝቦች በኑሮ ውድነት እየተጠበሱ የወያኔን ባለሥልጣናት ግን እህሉን ለውጭ ድርጅት እየቸበቸቡ መሆኑን የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ።

የወያኔ ባለሥልጣናት በስውርና በግልፅ ከተለያዩ የሐገሪቱ ክፍሎች በውድ ዋጋ ገዝተው ንብረትነቱ የእንግሊዝ ዜግነት ያለው ግለሰብ ድርጅት ለሆነው በውጭ ምንዛሪ እየሸጡ መሆኑን የገለፁት ውስጥ አዋቂ መንጮች በዚህ ስራ ላይ ከመለስ ዜናዊ ባለቤት ወ/ሮ አዜብ መስፍን ጀምሮ ከፍተኛ ባለሥልጣናት በሙሉ እጃቸው እንዳለበት አጋልጠዋል።

አንድ ኩንታል 1350 ብር ሆኖ ህዝቡ የመግዛት አቅም በሌለው በዚህ ወቅት እንኩዋን የወያኔ ሹማምንት በድብቅና በግልፅ ጤፍና ሽንብራ ከየገጠሩ በውድ ዋጋ እየሰበሰቡ ወደ ውጭ ሀገር መላካቸው እጅግ የሚያሳፍርና የሚያሳዝን ነው ያሉት አንድ ስማቸው እንዲገለፅ ያልፈለጉ ኢትዮጵያዊ በአሁን ሰዓት ያለው የኑሮ ዋጋ ንረት ከመቼውም ጊዜ በላይ ከቁጥጥር ውጭ እየወጣ ነው ሲሉ በምሬት ገልፀዋል።

የወያኔ ቡድን ለእንግሊዝ ኩባንያ ጤፍ መቸብቸቡን ያረጋገጡ ሁለት ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች እነሱም በተመሳሳይ ዋጋና ሁኔታ ለመግዛት እና በምትኩ ለሕዝቡ በነፃ ስንዴ በራሳቸው ገንዘብ ገዝተው እናከፋፍል ብለው ጥያቄ ቢያቀርቡም ለምን ሚስጥራችንን አወቁብን በሚል የተበሳጨት የወያኔ ባለሥልጣናት ባለሀብቶቹን ከሀገር እንዲወጡ ያስደረጓቸው መሆኑን ምንጮቹ አጋልጠዋል።

ሁለቱ ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች በቅርቡ ወደ ሀገር ቤት ገብተው ለእንግሊዙ ኩባንያ ጤፍ እየተሸጠለት መሆኑን በማስረጃ በማስደገፍ አቅርበው ይህንን እድል እኛ ኢትዮጵያውያኖች እንጠቀምበት በምትኩ ግን ለሕዝቡ ስንዴ ገዝተን በነፃ እናከፋፍል ብለው ጥያቄ ቢያቀርቡም በወያኔው መሪ መለስ ባለቤትና በስብሀት ነጋ ትዕዛዝ ወደ ውጭ እንዲባረሩ መደረጋቸውን ምንጮቹ አጋልጠዋል።

ሕዝቡ በረሀብና በኑሮ ውድነት እያለቀ መሆኑን እያወቁ ያለአንዳች ይሉኝታና ሀፍረት ጤፍና ሌሎች ጥራጥሬዎችን ለውጭ ሀገር ኩባንያዎች መሸጣቸው ለሕዝቡ ካላቸው ንቀትና ጥላቻ የተነሳ መሆኑን ያሳያል ሲሉ አንድ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ በንዴት ገልፀዋል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ፀጥታ አስከባሪ ኃይል አንሚ ሩጫየን ጨርሻለሁ ብሎ ድንበሩን ለቅቆ ከወጣ ወዲህ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ወታደራዊ ውጥረቱ አይሎ እንደሚገኝ የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል።

በተለይም በሻዕቢያ በኩል ቀድሞ የሌለውን የአየር ኃይል ይዞታ በውጭ ሀገር አብራሪዎች በመታገዝ እየተዘጋጀ መሆኑን የገለፁት ምንጮች ኢሳያስ በየጊዜው ወታደራዊ የጦር አለቆቹን እየሰበሰበ እንደሚያነጋግራቸው ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

በወያኔው በኩልም ወታደራዊ ዝግጅቱ እጅግ በተጠናከረ መልኩ የቀጠለ ሲሆን፣ መለስ ዜናዊም ሰሞኑን በምስጢር በቤተ መንግስት ውስጥ ጄኔራሎችን ሰብስቦ መወያየቱንና መመሪያ መስጠቱን የቤተ መንግስት ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል፡፡

ባለፈው ሳምንት አርብ እለት ከምሽቱ 2 ሰዓት በኋላ ወደ ቤተ መንግስት ገብተው ከመለስ ጋር ውይይት ያደረጉት የወያኔ ጄኔራሎች ከ2 ሰዓት ቆይታ በኋላም እንደወጡ ይኸው የውስጥ አዋቂ ምንጮች ዘገባ ያስረዳል፡፡

በሰሜን ከሻዕቢያ፣ በጐንደር ከታጣቂ ጋር፣ በምስራቅ ኦጋዴን ከተቃዋሚ ኃይል ጋር እየተፋለመ መያዥ መጨበጫ ሲጠፋው መሀል ያለውን ንፁሀን ዜጐች እያፈሰ ወደ እስር ቤት እያጋዘ ይገኛል ያለው የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ ሁሌም ሽንፈቱን የሚወጣው ንፁሃን ዜጐች በማሰርና በማዋከብ መሆኑን ጠቅሰው የወያኔ ቡድን አሁንም ውጥረቱ በሁሉም አቅጣጫ ሲያይልበት የሕዝቡን የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ሲል ብቻ መሀል ሀገር የሚኖረውን ሕዝብ በኑሮ ውድነት፣ በረሀብ፣ በእስራትና በሌሎችም መንገዶች እየተጠቀመ አንገቱን እንዲደፋ እያደረገ መሆኑንም ምንጮች አጋልጠዋል፡፡

የወያኔ በድን የስልጣን እድሜውን ለማራዘም ሲል ብቻ ፍቅር ከያዘው ከቻይና በርካታ የተለያዩ ዓይነቶች የጦር መሣሪያ እየሸመተ ወደ ሀገር ውስጥ እያስገባ ይገኛል ያሉት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ሰሞኑን የገቡት ቻይና ሰራሽ ከባድ መሣሪያዎች አጠቃቀማቸው እንኳዋን ሳይታወቅ በቀጥታ ወደ አውደ ውጊያው የወሰዷቸው መሆኑን ምንጮች ገልፀዋል፡፡

የወያነ አገዛዝ ሕዝብን ትጥቅ ለማስፈታትና ተስፋ ለማስቆረጥ በሚያካሂደው ዘመቻ የሚተባበሩ ኢትዮጵያውያን ቅጥረኞችከ ባዕድ ሀገሮች ወደ ኢትዮጵያ መጓዛቸው ተጋለጠ

ከ ሰሜን አሜሪካ፣ አውሮጳ፣ ኒውዚላንድና አውስትራሊያ ወደ ሀገር የተመለሱት እነዚህ የወያኔ ቅጥረኞች በአዲስ አበባ፣ ጎንደር፣ ባሕር ዳር፣ ሐረር፣ ድሬዳዋ፣ጂማ ወዘተ ወደ ዘመድና ሌሎችም ኢትዮጵያውያን ጋ በመሄድ ሀገር ወዳድ ድርጅቶችን በማጥላላት፣ ተከፋፍለዋል አይረቡም በማለት፣ወዘተ ዜጎች ተስፋ ቆርጠው ለወያኔ ድጋፍ እንዲሰጡ ወይም ለወያኔ እንደር ከሚሉ ከሀዲዎችና አን ጃዎች ጋር እንዲተባበሩ ለማድረግ እየጣሩ ነው ተብሏል፡፡ ለዚህ ዘመቻ የወያነ አገዛዝ ብዙ ገንዘብ መድቧል ሲባል ተላላኪዎቹ ደግሞ ራሳቸውን ፀረ ወያኔ አስመስለው በመቅረብ ለማደናገር መሞከ ራቸውም ተደርሶበታል፡፡ በርከት ያሉት ወደ ጎንደር የተላኩ ሲሆኑ መልዕክታቸውም የወያኔ አገዛዝ ለሱዳን መሬት አልሰጠም፣ሰጠ የተባለው ውሸት ነው ለማለትና በትግል ላይ ያሉትን ድርጅቶች ለማጥላላት ነው ተብሏል፡፡ በመሆኑም ዜጎች የእነዚህን የወያኔ መልዕክተኞች ተንኮል በማወቅ ነቅተው እንዲቋቋሙ ያስፈልጋል ተብሏል፡፡